# ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች የወጣውን መመሪያ ቁጥር 66/2004 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 88/2006

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ጥቅምት 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም የወጣውን መመሪያ ቁጥር 66/2004 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 88/2006

ያለውጭ ምንዛሪ ለቤተሰብ፣ለዘመድና ለጓደኛ ከውጭ አገር የሚላኩ በስጦታና በልገሳ የሚገቡ ያገለገሉ አልባሳት በጤና እና በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪው ላይ የፈጠሩትን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ፣

በስጦታና በልገሳ የሚላኩ ዕቃዎች መጠን ያለመወሰኑ በሕጋዊ ነጋዴ ተፎካካሪነት ላይ የፈጠረውን አሉታዊ ተፅዕኖ መቀነስ በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በደንብ ቁጥር 88/1995 0አንቀጽ 3(1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይኸን የተሻሻለ መመሪያ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች የወጣውን መመሪያ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 88/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ማሻሻያ</u>

   1. የመመሪያው አንቀጽ 5 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተተክቷል።

      5. <u>ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚገቡ ዕዎቃች</u>

         1/ ከመመሪያው ጋር ተያይዞ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት በዓይነትና በመጠን የሚወሰን ሆኖ ተራ ቁጥር 10 የተገለፁት ዕቃዎች፦

         ሀ. ጠቅላላ የ"FOB" ዋጋቸው ከ1000 USD /አንድ ሺህ ዶላር/ ድረስ በስጦታ ወይም በልገሳ የተላከ ዕቃ ማስገባት የሚቻል ሆኖ ነገር ግን ያገለገሉ አልባሳትን እና ጫማዎችን ማስገባት አይፈቀድም።

         ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) በተገለፀው መጠን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ2 (ሁለት) ጊዜ በላይ በስጦታ ወይም በልገሳ የተላከ ዕቃ ወደ አገር ማስገባት አይቻልም።

         ሐ. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለመመሪያው አፈጻጸም ተገቢውን መረጃ የመያዝና በዚሁ መሰረት የመፈጸም አላፊነት አለባቸው።

3. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣ ከ10 ቀናት በኋላ በተጫኑ ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

በከር ሻሌ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር